የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No 34.
ADDIS ABABA 7th June, 2007

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፮፻፲፱

CONTENTS

Proclamation No. 531/2007

Special Government Bond Proclamation Page 3619

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፩/፲፱፻፺፱

## ስለልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች /ቦንዶች/ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ለማሳደግ የሚውለው ገንዘብ በልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ /ቦንድ/ እንዲከፈል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ፡

፩/ ብር ፪.፭ ቢሊዮን ዋጋ ያለው ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ እንዲያወጣ፣

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል ለማሳደግ እንዲያውል፣

በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## PROCLAMATION NO. 531/2007.

## A PROCLAMATION ON SPECIAL GOVERNMENT BOND

**WHEREAS,** it has become necessary to issue special Government bond to be used for raising the capital of the Commercial Bank of Ethiopia;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Special Government Bond Proclamation No. 531/2007."

**2. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered:

1/ to issue special Government bond in the amount of Birr 2.5 Billion,

2/ Utilize the Special Government Bond issued in accordance with this Proclamation to raise the capital of the Commercial Bank of Ethiopia.

## ክፍል ሁለት
## ክፍያና ወለድ

### ፫. ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚወጡት ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ በ፲ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተከፍለው ይጠናቀቃሉ።

### ፬. ወለድ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡት ልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች ወለድ አይከፈልባቸውም።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ

### ፭. ከቀረጥና ግብር ነፃ መሆን

ከልዩ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶች /ቦንዶች/ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ወይም ሰነዶች ላይ የቴምብር ቀረጥ ወይም ሌላ ማናቸውም ቀረጥና ግብር አይከፈልም።

### ፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## PART TWO
## REDEMPTION AND INTEREST

### 3. Redemption

Special Government Bonds issued in accordance with Article 2 above shall be redeemed in 10 years period commencing from the time the bonds are issued.

### 4. Interest

Special Government Bonds issued in accordance with this Proclamation shall bear no interest.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS

### 5. Exemption From Taxes

No Stamp duty or any other tax shall be levied on any transaction or document relating to the Special Government Bonds.

### 6. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ